የሰ/መ/ቁ. 64819

ሰኔ 30 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሴ

አሊ መሀመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን - ዐቃቤ ህግ ገብረሚካኤል ወልዴ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ አንተነህ ካሣዬ - አልቀረቡም

መዝገቡን ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክስ ሲሆን አመልካች በአሁኑ ተጠሪና በሌላ የእቃው ባለቤት በተባለ ግለሰብ ላይ በቀረበው ክስ የወንጀል ህግ ቁ 32/1/ሀ/ እና የገቢዎችና ጉምሩክ አዋጅ ቁ 622/2001 አንቀጽ 91/2/ በመተላለፍ የጉምሩክ ስነ - ሥርዓት ያልተፈፀመባቸውን የተለያዩ አልባሣት ባጠቃላይ ለመንግስት ሊከፍል የነበረው ቀረጥ እና ታክስ 26,576 ብር ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-04051 ደሕ የሆነ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለቤትና ሹፌር በመሆኑ የተከሠሠ ሆኖ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በተከሠሠበት የህግ አንቀጽ ጥፋተኛ አድርጎታል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የደቡብ ክልል የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ በተከሠሠበት አንቀጽ ጥፋተኛ ካደረገው በኋላ የአሁኑ ተጠሪ በ7/ ሰባት/ ዐመት ፅኑ እሥራት እና በ5000/አምስት ሺህ / ብር እንዲቀጣ በመወሰን ከላይ የተመለከተው ተሽከርካሪ ለባለቤቱ እንዲመለስ ትዕዛዝ ሠጥቷል፡፡ የአሁኑ አመልካች በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ያስቀርባል በማለት ሲመለከተው ከቆየ በኋላ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 195/2/ ለ/ 2/ መሠረት አፅንቶታል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች በቀን 21/5/2003 ዓ.ም በ2 ገፅ በመፃፍ ያቀረበው የቅሬታ ፍሬ ሃሣብ ፡- ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበት አዋጅ ቁ 622/01 አንቀጽ 91/2/ ስንመለከት የእሥራትና የገንዘብ መቀጫው ሊጣል የሚችለው ወንጀሉ የተፈፀመበት ዕቃና መሣሪያ እና የወንጀሉ ፍሬ መወረሱ እንደተጠበቀ መሆኑን የሚደነግግ በመሆኑ ፣ ተጠሪ ደግሞ የመኪናው ባለቤትና በወቅቱ ሹፌር መሆኑን ራሱም ከማመኑ በተጨማሪ በማስረጃም የተረጋገጠ ሆኖ ሣለ ዕቃውን ሲያጓጉዝ የነበረው የተጠሪ መኪና እንዲወርስ መታዘዝ ሲገባው መታለፉ ያለአግባብ በመሆኑ፣ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 104/1/ የጥፋተኛነት ውሣኔ ከተሠጠ ተጨማሪ

ትዕዛዝ መስጠት ሣያስፈልግ ዕቃው ወይም ማጓጓዣው እንዲወረስ ይደረጋል በማለት የደነገገ ቢሆንም የሥር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሣኔ የሠጡ ቢሆንም ተሽከርካሪው እንዲወርስ ባለማዘዛቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የፈፀሙ በመሆኑ፣ ተጠሪ በቀጥታ በወንጀሉ ተሣታፊ በመሆኑ መኪናውን ከመወረስ የሚያስቀር አግባብ ሣይኖር የሥር ፍ/ቤቶች መኪናው ለባለቤቱ ይመለስ በማለት የሠጡት ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ እንዲታረምልን የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መጥሪያ ደርሶት ግንቦት 08 ቀን 2003 ዓም በ4 ገፅ ፅፎ ያቀረበው የመልስ ፍሬ ሃሣብ አመልካች የጠቀሳቸው የህግ አንቀጾች የተገለፀው ተሽከርካሪ እንዲወርስ የሚደነግግ አይደለም ፣ በተጠቀሰው አዋጅ 622/2001 አንቀጽ 91/2/ ዕቃና መሣሪያ የሚለው በእንግሊዝኛው /goods & equipment / ተብሎ የተተረጎመ በመሆኑ መኪናን አይጨምርም፣ የተላለፍኩት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ባለመኖሩ መኪናው ሊወረስ አይገባም ፣ የቀረበው ክስ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 91/2/ በመሆኑ እና በአዋጅ አንቀጽ 104/1/ መሠረት መኪናው እንዲወርስ የቀረበብኝ ክስ ሣይኖር የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት ስለሌለው ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ ቀርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም፡- በወንጀል ክሱ የተመለከተውን የኮንትሮባንድ ዕቃ ስታጓጉዝ የተገኘችው የተጠሪ መኪና ልትወርስ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለው ጭብጥ ተይዞ የተያዘው ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግንተነዋል፡፡ በዚሁ መሠረት እንደሚከተለው ተመርምሮአል፡፡ ተጠሪ ስያሽከረክረው የነበረው መኪና ኮድ ቁ 3-04051 ደሕ የሆነ የህዝብ ማመላለሻ ሚኒባስ የራሱ የግል ንብረት የሆነ መሆኑ፣ ሁለተኛ ተከሣሽ በነበረና በመኪናው የተሣፈረ ሰው የተጫነ የኮንትሮባንድ ዕቃ ለመንግስት ሊከፈል የሚገባ ታክስ እና ቀረጥ ከ21,791.66 ብር ያልተከፈለበት ሲያጓጉዝ በፖሊሶች መያዝ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ረገድ ያረጋገጠው ከመሆኑም አልፎ የጥፋተኝነት ውሣኔ እና ቅጣት በተጠሪ ላይ የተጣለ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በዚሁ ፍርድ ቤት የተሠጠው የጥፋተኝነት ፍርድ እና ቅጣት ስለመለወጡ በተጠሪ በኩል የተመለከተ ነጥብ የለም፡፡

የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁ 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት መሠረታዊ የህግ ስህተት ማረም በመሆኑ ማስረጃን የመቀበል እና የመመዘን ሥልጣን የበታች ፍርድ ቤቶች ሥልጣን በመሆኑ በዚህ ረገድ /በፍሬ ነገር / በበታች ፍርድ ቤት የተደረሰበትን መደምደሚያ መቀበሉ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ይሄ ከሆነ ደግሞ በተጠሪ ላይ የተላለፈው የጥፋተኝነት ውሣኔ በተሽከርካሪው መወረስ አለመወረስ ጋር ተያይዞ የሚያስከትለው ውጤት ምን እንደሆነና የበታች ፍርድ ቤቶች መኪናው ለባለቤቱ /ለተጠሪ/ ይመለስ ማለታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ ማየቱ ተገቢ ነው፡፡ ተጠሪዎች የተከሰሱበት የኮንትሮባንድ ወንጀል በአዋጅ ቁ 622/2001 አንቀጽ 91/2/ ወንጀሉ የተፈፀመበት ዕቃ ፣መሣሪያ እንደዚሁም የወንጀሉ ፍሬ የሚወረስ መሆኑ እና በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2/1/ ሥር ዕቃ ለሚለው ቃል ተንቀሣቃሽ ንብረት /መኪና/ በመጨመር ከመደንገጉም በላይ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 104/1/ መሠረት ደግሞ የተሽከርካሪ ባለቤትና ሹፌር ሆኖ

ተጠሪ ሲያሽከረክር በተፈፀመ የኮንትሮባንድ ወንጀል ጥፋተኛ መባሉ ተጨማሪ ትዕዛዝ መስጠት ሣያስፈልግ ወይም ተጠሪ እንደሚከራከረው በአመልካች ላይ ሌላ ክስ ማቅረብ ሣያስፈልግ መጓጓዥው እንዲወረስ መታዘዝ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ይሄ ከሆነ ጉዳዩን በመጀመሪያ የወንጀል ክሱን የተመለከተው ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሲሠጥ ወንጀሉ የተፈፀመበትን የተጠሪ ተሽከርካሪ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ማዘዝ ሲገባው ለባለቤቱ ይመለስ ማለቱ የአዋጁን ግልፅ ድንጋጌ ፣ ዓላማና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሠጥተናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የደቡብ ብሔ/ብ/ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ 39555 በቀን 24/3/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 12612 የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጡት ውሣኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 195/2/ መ/ መሠረት ተሻሽሎአል፡፡
2. በተጠሪ ስመንብረት ተመዝግቦ የሚገኘው የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-04051 ደሕ የሆነች ህዝብ ማመላለሻ ሚኒባስ የኮንትሮባንድ ወንጀል የተፈፀመበት ተሽከርካሪ በመሆኗ በመንግስት እንድትወርስ በማለት ታዟል፡፡
3. ተጠሪ የተሠጠውን ውሣኔ እንዲያውቀው በአርባ ምንጭ ማረሚያ ቤት በኩል ይተላለፍላቸው ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ